# አየር ንብረት፣ውሃ
# እና የኑሮ ዘይቤ



**የምስራቅ አፍሪካ ደረቅ (በረሃማ ወይም ዝናብ አጠር) ቦታዎች የአየር ንብረት ለውጥ ዋና መገኛዎች ተብለው ይጠራሉ፡፡**

- አማካይ የሙቀት መጠናቸው ቀስበቀስ እየጨመረ ሲሆን ይህም በአለም ላይ በሚገኙ ዝናብ አጠር ቦታዎች ላይ ፍጥነቱ እየጨመረ ይመስላል፡፡

- ዝናብ የሚዘንብበት ግዜ መለዋወጥ አይቀሬ ሲሆን ይህም የአየር ሁኔታን በቀላሉ ለመገመት እንዳይቻል ያደርገዋል፡፡

- አካባቢው እንደ ድርቅ እና ጎርፍ ባሉ ከባድ የአየር ለውጦች ሊጠቃ ይችላል፡፡



**ይህ የሚያሳው በአፈር ውስጥ የሚገነው የውሀ መጠን የማያስተማምን እየሆነ መምጣቱን ነው፡፡ ይህም፡-**


- የግጦሽ መሬት ሰብሎችና እንስሳት ላይ ተጽእኖ ያሳደርራል

- ሌሎች የአካባቢ ላይ ተጽእኖችን በመፍጠር እንደ ፕሮሶፒስ (በተለምዶ የወያኔ ዛፍ) እንዲስፋፋ ያደርጋል

- የASSAR ጥናት የሚያተኩረው አየር ንብረት ለውጥ ብቻውን መታየት እንደሌለበት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች መነሳት እንደሚኖርባቸው ነው፡፡




- ለምሳሌ ድርቅ የሚከሰተው በአየር ሁኔታ ለውጥ ብቻ ሳይሆን ሰዎች ለግጦሽ መሬትና ውሃ ያላቸው የአጠቃቀም ሁኔታም ይወስነዋል፡፡



- የአየር ንብረት ለውጥ ውጤቶችን እንዲሁም ሰዎች ከተለዋዋጭ አካባቢዎቸው ጋር ለመላመድ የሚሰጡትን ምላሽ በትክክል በመረዳት በኑሮአቸው የሚያጋጥማቸውን መሰናክሎች በግልጽ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

- ለውጥን መላመድ በተለያዩ ምክንያቶች ይወሰናል፡፡ እነዚህም፡-

  - የገቢ ምንጭን ማስፋፋት
  - የእንስሳት ወይም ሠብሎችን አይነት መቀያየር
  - ለስራ ወደሌሎች ቦታዎች መጓዝ
  - ማህበራዊ የመረዳዳት ልምዶችን ማጎልበት



**የእነዚህን ሁኔታዎች ውጤታማነት እንደሰዎቹ ፆታ፣ እድሜ እና ማህበራዊ ተሳትፎ ይወሰናሉ፡፡**

**ለእነዚህ ጉዳዮች ተገቢውን መልስ ለመስጠት የተለያዩ ድርጅቶችን፣ ዘርፎችንና በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ አካላትን ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡**

**ለምሳሌ፡-**

- የተለያዩ የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች በተለዋዋጭ ሁኔታዎች ውስጥ የሚያደርጉትን የተፈጥሮ ሃብት ሽሚያ እንዲቀንሱ መረዳት

- ውሀ ለተለያዩ ተጠቃሚዎችና አገልግሎቶች በመላው የአዋሽ ስምጥ ሸለቆ መዳረሱን ማረጋገጥ



# ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር መኖር




**የ ASSAR ጥናት የሚጠይቀው፡- በተለያየ የህብረተሰብ ክፍል እና የእድሜ  ደረጃ ላይ የሚገኙ የአፋር ወንዶችና ሴቶች ከአካባቢያቸው ሁኔታ ጋር ራሳቸውን ለማስማማት በቤታቸው ውስጥ ምን አይነት የለውጥ ስራዎች ይሰራሉ?**

- የአፋር አርብቶ አደሮች አየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋምና ለማላመድ 3 ዋና ዋና ተግባራት እያከናወኑ እንደሆነ ተረድተናል፡፡

- ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዘው የሚመጡ የደህንነት አደጋዎችን ለመቀነስ ከቦታ ቦታ የሚያደርጉትን ዝውውር ጨምረዋል (ውሃና የግጦሽ መሬት ፍለጋ)

- የአርብቶ አደር የሕይወት ዘይቤን በመተው ወደ አርሶ አደርነት የሚቀየሩ እና በደሞዝ  የሚሰሩ ሰዎች እየበዙነው

- የገቢ ምንጮቻቸውን እያስፋፉ ነው



- ወንዶች: ሴቶች እንዲሁም ወጣቶችና አዛውንቶች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚያደርሱባቸው ጉዳቶች ያለያያሉ፡፡ በተለይ በከተሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ህልሞቻቸውን እውን ማደረግ እያቃታቸው ተስፋቸው እየጨለመባቸው ይገኛሉ፡፡

- ወደ አዲስ ስራ መግባት ከባድ ውሳኔን ይጠይቃል፡፡ አንዳንድ ግዜ ቤተሰብ ሁለት እና ከዚያ በላይ መከፋፈል ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ሰዎችን ከቦታ ቦታ መዘዋወር የማይጠይቅ እና በአየር ንብረት ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ አዲስ ኑሮ መጀመር ከባድ ሊሆንባቸው ይችላል፡፡

- ድርቅ በሚሆንበት ግዜ ቦታ መቀየር አለመቻል በተለይ በሴቶችና አረጋውያን ላይ ከባድ ጫናን ይፈጥራል፡፡

- በተፈጥሮ ሃብት ላይ እንዲሁም በአየር ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የስራ እድል ለመፍጠር ከዚህ የበለጠ እርዳታ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም የሰዎችን አቅም በማጎልበት ተለዋዋጭ ሁኔታን ተቋቁመው ለመኖር ይረዳቸዋል፡፡



**ከእርሻና አርብቶ አደር ስራዎች ውጭ ያሉ እንቅስቃሴዎች የሚያጠቃልሉት፡-**
- ከተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ ጋር የሚሄድ ስልጠና መስጠትና ስራ እድል መፍጠር
- የብድር እና መነሻ ሂሳብ (ካፒታል) የሚገኝበትን መንገድ በማመቻቸት ሰዎች በጥቃቅን ስራዎች (ንግድ ዘርፎች) እንዲሰማሩ ስልጠና እና መመሪያ መስጠት

**በእርሻና አርብቶ አደር ስራዎች ላይ መቀጠል ለሚፈለጉ የሚደረጉ ድጋፎች**
- ድርቅን መቋቋም የሚችሉ የእንስሳት ዝርያዎችን እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዲሁም ዝናብ በሚያገኙበት ግዜ በቶሎ የሚያፈሩ የአዝዕርት አይነቶችን ማቅረብ
- እንደ ወያኔ ዛፍ (ፕሮሶፒስ) ያሉ ተክሎች እንዳይራቡ ማድረግ
- የግብርና የመድን ዋስትናን በማቅረብ በአነስተኛ ወጪ ውሃ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ እንደ የጠብታ መስኖ እና በዝናብ ውሀ እህል ማምረት ያሉትን አሰራሮች ማስተዋወቅ

**የሁሉንም የመቋቋም አቅም ለማጎልበት ማድረግ ያለብን፡-**
- እንደመብራት፣ ውሀ፣ እናቶችን ያካከተ የጤና ሽፋን የመሳሰሉ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማሻሻል
- ውጤታማና ህብረተሰብ ተኮር መርሀ ግብሮችን በመዘርጋት ቤተሰቦችን የአየር ንብረት ለውጥ ከሚያደርስባቸው ጫና እንዲወጡ መርዳት
- ውሃ የሚገኝባቸውን መንገዶች ማስፋፋት



በስራችን ሰዎችን በተለያዩ መልኩ ለማገዝ እንሰራለን፡፡
እነዚህም፡-

- ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር በመስራት ሰዎች እንዴት በተለዋዋጭ አየር ፀባይ ውስጥ እንደሚኖሩ በዚህም ሳቢያ የሚደርሱባቸው ተለያዩ ጫናዎች በዚህም ውስጥ ደግሞ ሴቶች፣ሕፃናት፣አዛውንት ይህንን ለመቋቋም ማድረግ ስለሚገባቸው ጉዳዮች በተሻለ እንዲረዱ ማድረግ

- ለምሳሌ  የፕሮሶፒስን መስፋፋት  እንዴት እንደሚገቱ  ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስልጠና በመስጠት እና አቅማቸው ማጎልበት

- እንደ ደህንነት የወጣቶች የስራ ተነሳሽነት እና ሰደት ባሉ ጉዳዮች ላይ የበለጠ ምርምር (ጥናት) ማድረግ



# ፕሮሶፒስ (በተለምዶ የወያኔ ዛፍ) ላይ ማተኮር



የዚህ አካባቢ ዋናው ችግር የፕሮሶፒስ (በተለምዶ የወያኔ ዛፍ) መስፋፋት ሲሆን ሰፊ አካባቢን በማዳረስ እና ጥቅጥቅ ብሎ  በመብቀል እድገቱን ከአመት ከአመት ጨምሯል፡፡

በጥናታችን የፕሮሶፒስን (የወያኔ ዛፍ) ችግር ለመረዳትና ችግሩን መግታት የሚያስችሉ የመፍትሔ ሀሳቦች ላይ ያተኮርን ሲሆን የተለያዩ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ለመመልከት ሞክረናል፡፡

- በ2013 ፕሮሶፒስ (የወያኔ ዛፍ) የአፋርን ክልል 3,605 ካሬ ኪሎ ሜትር እንዳደሚሸፍን ይታሰብ የነበረ ሲሆን ይህም ወደ 5,024 ካሬ ኪሎ ሜትር  ማደግ ችሏል፡፡ ይህ አሀዝ የተመሰረተው ለፕሮሶፒስ (የወያኔ ዛፍ) እድገት አመቺ በሆነው የመሬት ሰፋት ላይ ነው፡፡

- ይህም ለፕሮሶፒስ (የወያኔ ዛፍ) እድገት አመቺ ከሆነው መሬት ከግማሽ በላይ በፕሮሰፒስ (የወያኔ ዛፍ) ተይዟል ማለት ነው፡፡ በአሚባራ ወረዳ በ1973 እና 2004 አመታት ውስጥ ይህ ተክል (ዛፍ) በአመት የ3 ካሬ ኪሎ ሜትር ቦታ መስፋፋት አሳይቷል፡፡ በ2020: 31% የሆነው የወረዳው አካል በዚህ ጎጂ ተክል ሊዋጥ ይችላል፡፡



**የASSAR ፕሮጀክት ስራ ላይ በነበረበት ወቅት የፕሮሶፒስን (የወያኔ ዛፍ) ሰርጭት ለማቆም የተለያዩ ዘዴዎች ላያ የተወያየን ሲሆን በተለይም ከውሀ አካላት አካባቢ ለማጥፋት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የተክሉን ጥቅሞች በማጥናት እና የሰዎችን አስተያየት በመቀበል ዛፉን ጥቅም ላይ ለማዋልም ተሞክሯል፡፡**

**በሰራንባቸው አካባቢዎች የሚኖሩት ህዝቦች የሚያመጧቸው የመፍትሄ መንገዶች የሚለያዩ ሲሆኑ የትኛውም መንገድ ቀጣይነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡**

- ሰዎች ተክሉ ሙሉ በሙሉ እንዲጠፋ ቢፈለጉም ይጠፋል ብለው ያመኑ ግን ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበሩ

- ብዙ መፍትሔዎች ላይ የተወያየ ቢሆንም  ያተኮርነው ከአስፈላጊ ቦታዎች ማጥፋት እና ፕሮሶፒሰን (የወያኔ ዛፍ) ጥቅም ላይ ማዋል ላይ ነው፡፡

- ነገር ግን አንዳንድ አካላት በተለይም መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ተወካዮች የተክሉን ሰርጭት ለመግታት ህብረተሰቡ ራሱ የሚያመጣውን የመፍትሔ ሀሳቦች የበለጠ መርጠዋል፡፡





**ከህዝቡ ጋር በነበረን ምክክር ፕሮሶፒሰን (የወያኔ ዛፍ) በተመለከተ ያገኘናቸው ሀሳቦች የሚያጠቃልሉት ፡-**

- በተለያዩ በታዎች ፕሮሶፒስን (የወያኔ ዛፍ) ለመቆጣጠር እንደየፍላጎቱ የተለያዩ ዘዴዎችን  መጠቀም

- በመሬት ጉዳዮች ላይ ከሚሰሩ ሰዎች ጋር በጎ ምክክርና ውይይት በማደረግ የተሻለ መንገድ የሚሉትን በመምረጥ የእያንዳንዱን ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዲረዱ ማደረግ

- የተለያዩ አካባቢዎችን ሁኔታ ሊወክል የሚችል ሀገር አቀፍ የሆነ ዘዴ በመያዝ የወረዳ አስተዳድሮች ሊሰሩበት የሚያስችላቸውን ስልጣንና ግብአት እስካላቸው ድረስ በየራሳቸው መንገድ መስራታቸው ጠቃሚ ነው




**በዚህም የፕሮሶፒስን (የወያኔ ዛፍ) ስርጭት ለመቆጣጠር በሚከተለው መንገድ እገዛ ለማድረግ እናቅዳለን ፡-**

- ከፌደራል መንግስት ጋር በመተባበር የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን አስተያየት እንዲያገኙ ማድረግና የጥናታችን ውጤት በፕሮሶፒስ  (የወያኔ ዛፍ) ስርጭት ላይ በሚሰሩት ስራ እንዲያግዝ ማድረግ

- የወረዳ ማህበረሰቦችን ሰልጠና በመስጠት የተለያዩ ፕሮሶፒስን   የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን እንዲረዱ ማድረግ እንዲሁም እንደ አፈር ጥበቃ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ

- በተለይ የፕሮሶፒስን (የወያኔ ዛፍ) ችግር በተመለከተ አዳዲስ የጥናት እቅዶችን በማዘጋጀት በአፋርና ሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች ውስጥ ቁጥጥር እንዲደረግበት መንገዶችን ማፈላለግ



# ለውጥን መቋቋም



ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሚያስፈልግውን ሀብት እንዲያገኝ በተለያዩ የመንግስት ክፍሎችና ዘርፎች የተቀናጀ ስራ መስራት ቢኖርበትም በአዋሽ ሸለቆ ውስጥ የሚኖሩና የሚሰሩ ህብረተሰቦች ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ተሳትፏቸው ምን እንዲሰራላቸው እንደሚፈልጉና በምን መልኩ እንዲሰራ እንደሚፈለጉ ማስረዳት ይኖርባቸዋል

የASSAR ጥናት (ምርምር) የሚያተኩረው በክልልና ሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋማት አብሮ መሰራት አስፈላጊነት ላይ ሲሆን በተጨማሪም የነዋሪው ህዝብ ላለው እውቀትም ትልቅ ዋጋ ይሰጣል፡፡ ይህም የተወሳሰቡ ችግሮችን ለመፍታት ይረዳል፡፡ እነዚህ ችግሮች፡-

- በክልሉ የሚፈሰውን የአዋሽ ወንዝ ውሀ ፍትሀዊ በሆነ መልኩ መጠቀም

- የግጦሽ መሬቶች መገኘትና አለመገኘት እንደ ፕሮሶፒስ ባሉ ተስፋፊና ጎጂ ዛፎች በአጠቃቀም ችግር ምክንያት ይወሰናል

- የድርቅን አደጋ መቀነስ - አብዛኞቹ አርብቶ አደሮች ከከብቶቻቸው ጋር በመጓዝ  ቤተሰቦቻቸውን ለረጅም ጊዜ ለመተው  እንደሚገደዱ ነግረውናል፡፡

- ግጭቶችን መፍታት - በግጦሽ መሬትና የውሀ እጥረት ምክንያት አርብቶ አደሮች ከተለመደ አካባቢያቸው ርቀው በሚሄዱበት ወቅት፣በተለይም በድርቅ ወራት ዕርስ በዕርስ ለከባድ ግጭት ይጋለጣሉ




በተለዋዋጭ የአየር ሁኔታ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደርን (አጠቃቀምን) በተመለከተ ከባድ ጥረቶች እየተደረጉ ሲሆን አሁንም መሰናክሎች አሉ

- የሀብት አጠቃቀም እቅድ ብዙ ጊዜ በተከፋፈለ እና ከላይ ወደታች በተዋረድ የሚሰራ ነው፡፡

- የመፍተድሄ ድጋፎች የሚቀረጹበት ወቅት ከአገሬው ሰው የሚመጣውን የመፍትሔ ሀሳቦች የመቀበሉ እድል አናሳ ነው

- ደካማ የሆነ የመሬት አጠቃቀም እቅድ መኖር



በስራችን የመንግስትን እንቅስቃሴ በሚከተሉት መንገዶች ለመደገፍ እናልማለን እነዚህም ፡-

- አገር አቀፍ ደረጃ ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር በመስራት የሀብት አጠቃቀም እቅድ ላይ በትብብር የመስራት ባህል ማዳበር

- በስራ ላይ የሚገኙ የተቋማት  አደረጃጀትን በማሻሻ

- የሀብት አጠቃቀምን በተሻለ  መልኩ ማቀናጀት

- በተለይም መገለል የሚደርሰባቸውን እንደ ሴቶችና ወጣቶች ያሉ የማህበረሰቦች ክፍሎች (ባህላዊ አየር ሁኔታ፣ የዝናብ ወቅት፣ እና ድርቅ ተንባዮችን ጨምሮ) ለአካባቢያቸው ያላቸውን ግንዛቤ ዋጋ በመስጠት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ማካተት

- በተለይም ከብሄራዊ የፕሮሶፒስ ታስክ ፎርስ እና አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር (PAPTF) ጋር በመሰራትና በተሳትፎ ጉዳዮች ላይ ማማከር





# መግቢያ



1. ASSAR የምርምር ፕሮጀክት (የጥናት መርሃ ግብር) በአፍሪካ እና ከእስያ በሚገኙ ከፊል ደረቅ አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦች ለአየር ንብረት ለውጥ እና ተያያዥ ችግሮች የሚያጋልጡቸውን ሁኔታዎች አጥንቷል፡፡



2. የዚህ መርሀ ግብር አንድ አካል በመሆን ኢትዮጵያ የሚገኘው አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ እና የኬንያው ናይሮቢ ዩንቨርስቲ እንዲሁም የእንግሊዙ ኢስት አንግሊያ ዩንቨርስቲ አክስፋም ጂቢ ኢትዮጵያ እና ኬንያ ውስጥ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡

3. የአኗኗር ዘይቤያቸውና የደህንነታቸው ከአየር ንብረት ጋር ከተቆራኙ አርብቶ አደሮች እና አርሶ አደሮች ጋር በመነጋገር ከተለዋዋጩ ከአየር ንብረት ጋር ራሳቸው እንዲያላምዱ የሚያግዟቸውን  ሁኔታዎች ነቅሰን ለማውጣት እንሰራለን፡፡





4. ይህ ጥንቅር እስካሁን ያገኘናቸውንም ምላሾች ለማጋራት ያለመ ሲሆን ሀሳብና እውቀትን በማስፋፋት በኢትዮጵያ የሚገኙ ማህበረሰቦች ፣ ሀገር በቀል ድርጅቶች እና መንግስታዊ ተቋማት በተሻለ መላኩ ህዝቦችን ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ለማላመድ መፃኢ እድላቸውን ብሩህና የተሻለ ለማድረግ እንዲሰሩ ያስችላል፡፡

5. በኢትዮጵያ እስካሁን በአብዛኛው በደቡባዊው የአፋር ክልል በሚገኙት አዋሽ ፈንታሌ እና አሚባራ ወረዳዎች ሰርተናል፡፡ በአራቱ አመታት የምርምር ቆይታ በ2 ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ 17 ማህበረሰቦች ካሉ 1,109 ሰዎች  ጋር ተነጋግረናል፡፡ በተጨለማሪም ከወረዳ፣ ክልል እና አገራዊ ደረጃ ከሚገኙ 84 ባለድርሻ አካላት ጋር ተነጋግረናል፡፡

6. ከዚህም የተረዳነው፡-

- ሁሉም ሰው ተመሳሳይ  በሆነ (የተጋላጭነት ደረጃ) ላይ እንዳልሆነና እኩል ምላሽ የመስጠት አቅም እንደሌለው
- ህዝቦች ዘለቄታ ያለው የገቢ ምንጭ ማግኘት ብቻ ሳይሆን የችግር አፈታት ውሳኔዎችንም የመግለጽ መብት እንዳላቸው
- ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ራስን ለማላመድ የመፍትሔ ሀሳቦች ከማስተዋወቃችን በፊት ሀሳቦቹን በተሳካና ፍትሀዊ በሆነ ሁኔታ እንዲተገበሩ ሊያግዙዋቸው ወይም ሊያደናቅፋቸው የሚችሉ ጉዳዮችን በቅድሚያ መገንዘብ እንደሚገባን ነው፡፡





7. ተከታዮቹ ዝርዝሮች የስራችንን ዋና ዋና መልክቶች የሚያጠቃልሉ ናቸው፡፡